## ምድብ አራት

## 17ኛ ሳምንት

# ቅዱስ ኒቆላዎስ - ሊቀ ጳጳስ (Santa Claus)

### የትምህርቱ ዓላማ

❖ ቅዱሳንን በሚገባ አውቀን እንድናከብራቸው እና እኛም እፍዚኣብሔርን እንዴት ደስ እንደምናሰኘው መማር።

### የሚጠና ጥቅስ

❖ *"የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።"ራእየ ዮሐንስ* 2፡10-11

### ምንባብ

❖ *መጽሐፍ ቅዱስ*(*የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ አንብብዋቸው*)፤*መጽሐፈ ስንክሳር* (*ታኅሣስ* 10)

### መግቢያ

❖ በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ በተከተለው ቅዱስ ኒቆላዎስ መንፈሳዊ ሕይወት ተመስርተን እንማራለን።

❖ ወደዋናው ትምሕርት ከመግባታችን በፊት ስለ ሳንታ ክላውስ (Santa Claus) የምታውቁትን ለመምህር አስረዱ።

### ልደቱ ዕድገቱ እና መንፈሳዊ አገልግሎቱ

❖ ኒቆላዎስ አባቱ ኤጲፋንዮስ እናቱ ዮና ይባላሉ።እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባዕለጸጎች ነበሩ።ልጅ ግን አልነበራቸውምና፤

❖ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሠጣቸው ሲለምኑ ኖረው መውለጃቸው ሲያልፍ እግዚአብሔር ልጅ ሠጣቸው።ስሙንም ኒቆላዎስ አሉት።

❖ ከሕፃንነቱ ጀምሮ በነበረው መንፈሳዊነት ሁሉም ይደነቁ ነበር።ትኩረቱንም መንፈሳዊውን ምግብ ቃል እግዚኣብሔርን መመገብ ነበር።እድሜው ሲደርስም ወላጆቹ የቤተክርስቲያንን ትምህርት እንዲማር ላኩት።

<u>*መንፈሳዊ አገልግሎቱ*</u> ትምህረቱን በሚገባ አጠናቆም ፣ መንፈሳዊ ሥራን በየቀኑ የሚጨምር ሆነ የአጎቱ ልጅ በአበምኔት ወዳለበት ቦታም ሄዶ በድንግልና መኖር ጀመረ።በፍጹም ተጋድሎ እየኖረም በ19ዓመቱ ቅስና ተቀበለ።እግዚአብሔርም ድንቅና ተዓምር መፈጸምን ድውያንንም የመፈወስ ጸጋ ሰጠው፤በተሠጠው ጸጋም፡-ከሰዎችና ከሚያመልኳቸው ዛፎች አጋንንት አወጣ፤በርካታ በሽተኞችንም ፈወሠ፤ትንሽ እንጀራ ባርኮም ብዙ ሕዝብ መገበ።

❖ በመጽሐፍ ቅዱስ ***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።***ዕብ.13፡3 ተብሎ እንደተጻፈም፤አራት ሴት ልጆች የነበሩትንና ከኃብታምነት ወደ ፍጹም ድኅነት የተሸጋገረን ሰው ረድቶል።**ታሪኩም እንዲህ ነው፡-**

❖ ይህ ሰው ሴቶች ልጆችን መዳርና መመገብ ስላቃተው።በዝሙት እንዲኖሩ ቤቱን የዝሙት ቤት ሊያደርግ ሲዘጋጅ አባ ኒቆላዎስ በእግዚኣብሔር ጸጋ አውቆ ወደዚህ ሰው ቤት በሌሊት ሄደ።ወንጌል ***ስጡ ይሠጣችሁማል፤በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላች/ልና*** ሉቃ.6፡38 እንዳለ በመጀመሪያ 100 ወርቅ ዲናር በበሩ ሥር አስቀምጦለት ተሰወረ።

❖ በዚህም ጌታችን ***አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ፤በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል፡***ማቴ. 6፡3-4 ያለውን ቃል ፈጸመ።ሰውየው ጠዋት ሲነሣ የወርቅ ዲናሩን አገኘና ፈጣሪውን አመስግኖ የመጀመሪያይቱን ልጅ ዳራት፤ለሁለተኛ እና ሦስተኛዋም አባ ኒቆላዎስ ተደብቆ ሰዉየዉን ረዳው ሰውየዉም እግዚኣብሔርን አመስግኖ ልጆቹን ዳረ።

❖ በመጨረሻም ሰዉየዉ ገንዘቡን የሚሰጠው ማን ? መሆኑን ለማወቅ ነቅቶ ሲጠብቅ ቅዱሱ እንደተለመደው ወርቁን አስገብቶ ሲሄድ ደረሰበት።አባ ኒቆላዎስ መሆኑን ሲያውቅም እግሩ ላይ ወድቀው ከልጁ ጋር አመሠገኑት።ወንጌል በዚህ ምድር ብቻ ከሰው የሚመሰገኑ ***ዋጋቸውን ተቀብለዋል*** እንዳለ ሰማያዊውን ዋጋ እንዳያስቀሩበት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ነግሮአቸው ሄደ።

❖ <u>ከዚያም በተነገረው ትንቢት ጵጵስናን ተቀበለ፤</u> በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ እና ጣኦት እንዲያመልኩ የሚያስገድድ አዋጅ ወጣ፤ቅዱስ ኒቆላዎስም ምዕመናን እግዚኣብሔርን በማመን እንዲጸኑ ያስተምር ነበር።በራእየ ዮሐንስ **" ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ።እንሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው።.........እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።መንፈስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።"** ራዕ.2፡10-11 ተብሎ እንደተነገረ።ዲዮቅስጥያኖስ ምንም ጥፋት ሳያገኝበት አቡነ ኒቆላዎስን በብዙ መከራ አሠቃየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደ ቅዱስ ቃሉ አጸናው፤ሥቃዩም አልጎዳውም።ማሰቃየቱ የሠለቸው ዲዮቅልጥያኖስም ቅዱሱን አሰረው።

❖ ለወዳጆቹ የሚፈርድላቸው እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ትዕግስት አስቦ ዲዮቅልጥያኖስ ተሸኘፎ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በሮም መንበረ መንግሥት ተተካ።***ሥራህን አውቃለሁ፤እነሆ.በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና.ስሜንም አልካድህምና።ራዕ 3፡8*** ተብሎ እንደተጻፈም።ቆስጠንጢኖስ ካስፈታቸው ቅዱሳን አንዱ ይህ ቅዱስ አባት አቡነ ኒቆላዎስ ነበር።ከእስር ወጥቶ ወደ ሌላው የሕይወቱ ምዕራፍ፤ጌታችን ወደ ከፈተለት የአገልግሎት በር ተሰማራ።

❖ ወደ መንበረ ጵጵስናው ተመልሶም ምዕመናንን እና አምላኩን በብርቱ አገለገለ።አርዮስ ሲነሣም በኒቅያ ጉባዔ ከነበሩት 318ቱ ሊቃውንት አንዱ ይህ ቅዱስ ነው።ከዚያም ያማረ ተጋድሎውን ፈጽሞ በጵጵስናው ብቻ ከ40 ዓመት በላይ አገልግሎ አረፈ።

### ምን ተማርን ?

1. ቅዱስ ኒቆላዎስ ፈጣሪዉን ከልጅነቱ ጀምሮ ተከተለው እግዚኣብሔርም በጸጋ ጎበኘው ከፍ ከፍም አደረገው።***የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ መክ.12፡1*** ተብለናልና እኛም እግዚኣብሔርን የምናገለግልበት ዘመን አሁን ነው።

2. ለሰዎች መልካም እናድርግ በተለይም ለተቸገሩ የልደት መልዕክትም ይሄው ነው፤ሁሉም የእርሱ የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት የተወለደው የተቸገረውን የሰው ልጅ ባለጸጋ ለመድረግ ነው፡፡ቅዱስ ጳውሎስ ***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ፡፡***ዕብ.13፡3 ብሎ እንዳስተማረን አቡነ ኒቆላዎስ ከተቸገረው ቤተሰብ እኩል ተጨንቆ የሚችለውን አደረገ፤እኛም የገና ሥጦታን ከቅዱሱ አባት በተማረነው መሰረት ማድረግ እንማራለን፡፡

3. "***በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው ከተፈተነ በ/ላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና፡፡*** "ያዕ.1፡12 ቅዱስ ኒቆላዎስ መመጽወት በሚችልበትና በሚመሰገንበት ግዜ ብቻ ሳይሆን በግርፋት እና እስራትም ስለጸና እግዚኣብሔር አከበረው፡፡እኛም በማንኛውም መከራ እግዚኣብሔር እንደማይተወን አውቀን መጽናትን ከአባታችን እንማራለን፡፡

4. የቅዱሳንን ታሪክና መልካም ተጋድሎ በተገቢው መንገድ ብናከብረው ከጻድቁ በረከት እናገኝበታለን፡፡***የጻደቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል - ለበረከትም ነው*** ፡፡ መዝ.111(112)፡6፤ምሳ.10፡7 የቅዱሳንን በዓላት በመንፈሳዊ መንገድ ማሰብ አለበን፡፡ምክንያቱም እግዚኣብሔር ቅዱሳንን የሰጠንና ቤተክርስትያንም የዘገበችልንና የምታስባቸው፡፡**እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፤እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን.የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን.በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ** ዕብ.12፡1-2 ስትለን ነው፡፡ቅዱሳን ክርስቶስን መስለውታልና 1ኛ.ቆሮ.11፡1 በተግባር ብንከተላቸው ክርስቶስን እናገኘዋለን፡፡

5. ቅዱስ ኒቆላዎስ (santa claus)የእምነት፤የልግስና፤የእውነት እና ለእግዚኣብሔር እና ለቤተሰብ የመታዘዝ ሕይወትን ያሳየ የመንፈሳዊው ተጋድሎም አርኣያችን ነው፡፡

ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን እኛንም በቅዱስ ኒቆላዎስ ጸሎት ይጠብቀን፡፡በረከቱም ትደርብን፡፡አሜን!!

## <u>እግዚአብሔርን ወደ መውደድ የሚመሩን ተግባራዊ መንገዶች</u>

<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>፡- ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚያሳድጉ እና የሚያጸኑ ተግባራዊ መንገዶችን መማር፡፡

<u>የሚጠና ጥቅስ</u> ፡-"***ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ፣ የተቀደሰ ስሙን፡፡***" መዝ. 102(3)፣1

<u>የትምህርቱ ትኩረት</u>

- ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር በዚህ ምድርም ሆነ በዘላለማዊ ሕይወታችን በደስታ መኖር ጠቃሚ ነው፡፡
- በዚህ ትምህርታችንም እግዚአብሔርን የበለጠ እንድንወደው ስለሚረዱን መንገዶች ትኩረት ሰጥተን እንማራለን፡፡
- እግዚአብሔርን የበለጠ ለመውደድ የሚረዱን መንገዶች

1) ሁሌም የእግዚአብሔርን በረከቶችና የሠጣችሁን ሁሉ አስታውሱ !

- እግዚአብሔር በፈለጋችት ሁሉ የረዳችሁን አስቡ፡፡ አሁን ላላችሁበት እንድትደርሱ ያገዛችሁ እርሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ባላችሁ ነገር ሁሉ (ቤተሰብ፣ ትምህርት፣ ጤና ….) የባረካችሁም እርሱ ነው፡፡
- ወደ ቤቱ እንድትመጡ ጠራችሁ፣ ቅዱስ ቁርባንን እንድትቀበሉና ሌሎች በረከቶችን እንድታገኙም ፈቀደላችሁ፡፡
- ከዳዊትም ጋር"***ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ፣ የተቀደሰ ስሙን፡፡" ብላችሁ*** የሚለውን አንብቡ፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሠጥቶናል ጤና፣ ቤተሰብ፣ የሚመራን መንፈስ ቅዱስ እና ምቾት…

2)ስትጸልዩ ፣ በሙሉ ልባችሁ ጸልዩ እንዲሁም የፍቅር ቃላትን ተጠቀሙ

- በጸሎታችሁ የምትናገሩትን አስቡት፣ ሌላ ነገርም አታስቡ
- ከልባች ጸልዩ፡፡ ስተጸልዩም እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁ፣ በልባችሁ እንዲያድርና በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞሉ ለምኑ፣ በፍጹም ልባችሁ እንድትወዱትም እንዲረዳችሁ አጥብቃችሁ ጽልዩ፡፡

3)ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በመታዘዝ እንጀምር፡፡

- ለእግዚአብሔር ስንታዘዝ፣ የተናገረንን እንፈጽማለን፤ በዚህም ደስታን እና በሕይወታችን ትርጉም እናገኛለን ይህም የበለጠ እግዚአብሔርን እንድናውቀውና እንድንወደው ያደርገናል፡፡

4) እግዚአብሔርን ለመውደድ ከፈለጋችሁ ስለርሱ አንብቡ ፣ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር ስጡ፡፡

- ስለእግዚአብሔር ለማወቅና ለማሰብ፡፡ ስለ እርሱ የበለጠ አንብቡ … ስለእርሱ ስታነቡና ስታስቡም አዕምሮኣችሁ እና ልባችሁ ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ጋር ይሆናል ትወዱትማላችሁ፡፡ ***"የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው በዚያን ጊዜም መንገድህን ይቃናልሃል ይከናወንልሃልም፡፡"*** ኢያ.1፡8

5) እግዚአብሔርን የበለጠ ለመውደድ እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ነገሮች አስወግዱ፡፡

- ከቁሳዊና ክፉ ነገሮች ራቁ ኃጢአትና ስድብም ተው፣ ወደ ሕይወታችሁ እንዳይገባም ተጠንቀቁ፡፡ ***"ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ በዓለም ያው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡"*** ዮሐ. 2፣15-16

6) ያጋጠማችሁ ችግር ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ አታስቡ፡-

- ***"ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡ "*** ያዕ. 1፣13
- እግዚአብሔር ክፉ ነገር አይሠጠንም፡፡ያጋጠሙን አሳዛኝ ነገሮች ሁሉ ምንጫቸው እግዚአብሔር አይደለም፡፡እግዚአብሔር መልካም ነው የሚሠጠንም መልካም ነገሮችን ነው፡፡ክፉ ነገር ሲያጋጥማችሁም እግዚአብሔርን አትውቀሱ፡፡ይህ የኃጢአታችንና የስህተታችን ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም የሌሎች ስህተት ችግሩን ፈጥሮብን ይሆናል፡፡
- መስቀሉን ካለማቋረጥ ተመልከቱ እግዚአብሔር ለሁሉም ያለውን ያልተገደበ ፍቅር አስቡ ***"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፡፡"*** 1ኛ ዮሐ. 4፣19

<u>ምን ተማርን ?</u>

1) ክርስትና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው ***"እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል"*** 1ኛ ዮሐ. 4፣16

2) ከላይ የተጠቀሱትን የምንፈጽመው ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንዲኖረን ነው፡፡

3) እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለው ዓለማ ፍቅር ነው፡፡እግዚአብሔር ትዕዛዝትን የሠጠን ለማዘዝ ብቻ አይደለም ወይም መንግሥተ ሰማያትን መውረስ አስቸጋሪ እንዲሆንብን አይደለም፡፡

4) በዙሪያችን ላሉ ሰዎች መልካም መሆንንና መውደድን መለማመድ አለብን፡፡ ይህም ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርስን መንገድ ነው፡፡

ይቆየን…….